

# ዋና ዋና ማጠቃለያ

## የሴት ልጅ ግርዛት በኢትዮጵያ:

ወቅታዊ ሀገራዊ መረጃ

ሰኔ 2015

28 TOO MANY
FGM... let's end it.

ORCHID PROJECT

ይህ የሀገር መግለጫ መረጃ በኢትዮጵያ (2015/16) ስለ ሴት ልጅ ግርዛት/ብልት ትልተላ (FGM/C) ወቅታዊ ሁኔታዎች እና መረጃዎች ላይ ሰፊ መረጃ ይሰጣል። እንዲሁም የወቅቱን የፖለቲካ ሁኔታና ይህንን ተግባር እንዴት ማስወገድ እንደሚቻል የሚያሳዩ የህግ ማዕቀፎችን እና መርሃ ግብሮችን ትንተናና ምክሮችን መስጠትን ያካትታል። ይህ ሪፖርት የ2013 ***(28 Too Many's 2013 Ethiopia Country Profile.)*** ማሻሻያ ሆኖ ያገለግላል። ዓላማውም በኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ላይ እጅግ የተሻለውን ወቅታዊ መረጃ በማዘጋጀት አክቲቪስቶችን፣ ባለሙያዎችን፣ የልማት አጋሮችን እና የምርምር ድርጅቶችን በፖሊሲ እና በተግባር ላይ የውሳኔ አሰጣጥን ለማሳወቅ ነው።

ኢትዮጵያ በአፍሪካ ፈጣን ኢኮኖሚ እያስመዘገበች ያለች ሀገር,[1] ብትሆንም በ UNDP **የማህበረሰብ ልማት መረጃ ጠቋሚ** መሰረት ከ191 ሀገራት 175 ("ዝቅተኛ ልማት") ደረጃ ላይ ትገኛለች።[2] ይህ እድገት በአገሪቱ ወደሉት በጣም ለችግር ተጋላጭ ወደሆኑት ህብረተሰብ አልወረደም።

**ጠቅላይ ሚንስትር አብይ አህመድ** በየካቲት 2010 ዓ.ም ስልጣናቸውን በለቀቁበት ጠቅላይ ሚኒስትር ደሳለኝ ምትክ በይፋ በሐምሌ 2013 ዓ.ም ሌላ ተክተው መርጠዋል።[3]

ኢትዮጵያ በታሪኳ ብዙ ፖለቲካዊ እና ባህላዊ ውዝግቦችን አስተናግዳለች፤ በቅርቡ በሰሜን ትግራይ ክልል ከ2012 እስከ 2014 ድረስ በቆየው ውዝግብ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን እና የተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብት ኮሚሽነር[21] ፅህፈት ቤት ዓለም አቀፍ የሰብአዊ/የስደተኞች መብቶች ጥሰት እና የጦር ወንጀሎች ማስረጃን አግኝተዋል።[22] በተጨማሪም በጥር 2015 ዓ.ም እምነታቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ እንዲያካሂዱ በሚገፋፉ መሪዎች ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተገንጥሎ በተቋቋመው አዲስ ሲኖዶስ ምክንያት ብጥብጥ ተቀስቅሷል።[23] የትምህርት ቤቶች መዘጋት፣ እንደ አስገድዶ መድፈር ያሉ የጦር ወንጀሎች፣ የጤና አገልግሎቶች እና እርዳታዎች መስተጓጎል እና አጠቃላይ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ አለመረጋጋት ተከስቷል።

ኢትዮጵያ በታሪኳ ብዙ ፖለቲካዊ እና ባህላዊ ውዝግቦችን አስተናግዳለች፤ በቅርቡ በሰሜን ትግራይ ክልል ከ2012 እስከ 2014 ድረስ በቆየው ውዝግብ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን እና የተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብት ኮሚሽነር[4] ፅህፈት ቤት ዓለም አቀፍ የሰብአዊ/የስደተኞች መብቶች ጥሰት እና የጦር ወንጀሎች ማስረጃ አግኝተዋል።[5] በተጨማሪም በጥር 2015 ዓ.ም እምነታቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ እንዲያካሂዱ በሚገፋፉ መሪዎች ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተገንጥሎ በተቋቋመው አዲስ ሲኖዶስ ምክንያት ብጥብጥ ተቀስቅሷል።[6]

## ብጥብጦች እና አለመረጋጋት በሴቶች እና ልጃገረዶች መብቶች ላይ፣ በውሳኔ ሰጪነታቸው እና በአጠቃላይ የአንድ ሀገር እድገት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖዎችን ያስከትላሉ፤ በዚህ ምክንያትም ለምሳሌ ያህል የትምህርት ቤቶች መዘጋት፣ እንደ አስገድዶ መድፈር ያሉ የጦር ወንጀሎች፣ የጤና አገልግሎቶች እና እርዳታዎች መስተጓጎል እና አጠቃላይ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ አለመረጋጋት ተከስቷል።

ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ በህገ መንግስቱ የታሰበውን የፕሬስ ነፃነት እውን ለማድረግ መጀመሪያ ላይ መሻሻል እንዲያሳይ አደርገው ነበር። አፋኙ የስርጭት/የብሮድካስቲንግ አገልግሎት አዋጅ በ2013 ዓ.ም የተሻረ ሲሆን አዲስ የሚዲያ ህግ በጋዜጠኞች ላይ የሚደርሰውን ህገወጥ እስራት ለመቀነስ አላማ አድርጎ ቀርቧል።.[7] በሚያሳዝን ሁኔታ ድንበር የለሽ ዘጋቢዎች እንደጻፉት ኢትዮጵያ በዘር ግጭት እና የእርስ በርስ ጦርነት ከተያዘች በኋላ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የታዩት የፕሬስ ነፃነት ግኝቶች አብዛኛዎቹ ጠፍተዋል።'[8] የተሳሳተ መረጃን እና በሰሜን ኢትዮጵያ የተነሳውን የትግራይ ግጭትን የሚቃወም አዲስ ህግ የመንግስት ኤጀንሲዎች እና የሚዲያ ባለስልጣናት ሚዲያውን እንደገና ማፈን እንዲጀምሩ ፍቃድ የተሰጠ ይመስላል።ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ስለታሰሩት የጋዜጠኞች ትክክለኛ ቁጥር ያለው ዘገባ ይለያያል፤ ነገር ግን ብዙ የተለዩ የእስር እና የጥቃት ምሳሌዎች አሉ።[10] የበይነመረብ መገናኛ ዘዴም ተገድቧል። [11] በከፊል በእነዚህ ክልከላዎች ምክንያት ሬድዮ በብዛት ተደራሽነት ያለው መካከለኛ[12] በመሆኑ አሁንም የኢትዮጵያን ህዝብ የሴት ልጅ ግርዛት እና ተያያዥ ጉዳዮችን ለማድረስ በጣም ውጤታማው መንገድ (ከመገናኛ ብዙኃን አንፃር) ራዲዮ ነው። እገዳው ከቀጠለ የኢትዮጵያ ህዝብ ጤና እና ደህንነት በእጅጉ ይጎዳል። በ1992፣ 1997፣ 2003 እና 2008 ዓ.ም በኢትዮጵያ የሴት ልጅ ግርዛት ስርጭት ላይ ያለው መረጃ በስነ ሕዝብና ጤና ዳሰሳ (DHS) ላይ ተጠናቅሯል።

በኢትዮጵያ የሴት ልጅ ግርዛት ስርጭት እየቀነሰ ያለ ይመስላል። እንደ DHS ዘገባዎች በ1992 ከ15-49 ከነበሩት 79.9% ሴቶች በ1997 ወደ 74.3% እና በ2008 ወደ 65.2% ዝቅ ብሏል።[13]

## ሆኖም የኢትዮጵያ ህዝብ ቁጥር እየጨመረ በመምጣቱ ለአደጋ የተጋለጡ ልጃገረዶች ቁጥር ጨምሯል።

ከ2016 ጀምሮ በኢትዮጵያ እስካሁን 33 ሚሊዮን ልጃገረዶች እና ሴቶች ለአደጋ ተጋላጭ እንደሆኑ የኦርካይድ ፕሮጀክት ግምት ያሳያል። ይህም በምስራቅ እና ደቡባዊ አፍሪካ ውስጥ እጅግ ትልቁ የልጃገረዶች/ሴቶች ቁጥር ሲሆን በአለም አቀፍ ደረጃ ከኢንዶኔዥያ እና ግብፅ ቀጥሎ ሰስተኛው ነው።

በምስራቅ ኢትዮጵያ (ሶማሌ እና አፋር) ከፍተኛ የሴት ልጅ ግርዛት ስርጭት ሲኖር ዝቅተኛው ደግሞ በትግራይ ሰሜናዊ ክልል ውስጥ ነው። ነገር ግን የህዝብ ብዛትን ከግምት ውስጥ በማስገባት ከ60% በላይ የሚሆኑት በግርዛት የተጠቁ ሴቶች እና ልጃገረዶች የሚኖሩት በኦሮሚያ (ዘጠኝ ሚሊዮን) እና በአማራ (ሰባት ሚሊዮን) ክልሎች ነው። ከ1992 እስከ 1998 ባለው ጊዜ ውስጥ ከፍተኛው መሻሻል/የስርጭት ቅነሳ የታየው በድሬዳዋ (95.1% ወደ 75.3%)፣ በአማራ (79.7% ወደ 61.7%) እና በአዲስ አበባ (79.8% ወደ 54%) ነው። ዝቅተኛ መሻሻል ያስመዘገበው ክልል ሱማሌ ነው (99.7% ወደ 98.5%)። [14]

የሴትን ልጅ ግርዛት አስከፊነት የሰሙ 17.5% ሴቶች እና 11.1% ወንዶች (ከ15-49 እድሜ ያላቸው) ድርጊቱ መቀጠል እንዳለበት ያምናሉ። 79.3% ሴቶች እና 86.7% ወንዶች ደግሞ መቀጠል እንደሌለበት ያምናሉ።[15]

ነገር ግን በተዘዋዋሪ መንገድ የአጠያየቅ ዘዴዎችን በመጠቀም በተደረጉ ትንንሽ ጥናቶች ላይ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች በቀጥታ ሲጠየቁ ለግርዛት የሚሰጡት ድጋፍ ዝቅተኛ መሆኑን ሲገልጹ፤ በተዘዋዋሪ ሲጠየቁ ግን የድጋፉ መጠን በላቀ ደረጃ ከፍ ያለ መሆኑን ያሳያል።[16]

## *እንደዚህ ያለው ጥንቃቄ የሚፈልግ፣ ሚስጥራዊነትን የተላበሰ እና በማህበረሰቡ ዘንድ በግልጥ ለማውረት ያልተፈቀዱ ጉዳዮች በሚመረምሩበት ጊዜ የተሻሻሉ የዳሰሳ ጥናት ዘዴዎችን አስፈላጊነት ያጎላሉ።*

በተለይም የሴት ልጅ ግርዛት ለጋብቻ ብቁ ከመሆን እና ከንጽህና ጋር የተቆራኘ ስለሆነ በሚያሳዝን ሁኔታ አሁንም በአንዳንድ የኢትዮጵያ ማህበረሰቦች ዘንድ የሴትን ልጅ ግርዛት አለመፈጸም አሉታዊ ተጽዕኖ አለው። አብዛኛዎቹ ልጃገረዶች እና ሴቶች እነዚያን መዘዞች ለማስወገድ ሲሉ የሴት ልጅ ግርዛትን ለመፈፀም ይነሳሳሉ።[17]

## በኢትዮጵያ ውስጥ የብሄር ማንነት እና ለዚያ ያለ ስምምነት የሴት ልጅ ግርዛት ጠንካራ አንቀሳቃሽ ነው።

ይህም የሴት ልጅ ግርዛት መስፋፋት እና መቀጠል አለበት የሚለው እምነት ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል።

ብሄር ከሀይማኖታዊ ትስስር ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነው፤ ስለዚህም የሴት ልጅ ግርዛት በዋና ዋና ሀይማኖቶች ይፈለጋል የሚለውን የተሳሳተ እምነት ከፍ ያደርጋል። በአገር አቀፍ ደረጃ ከ15-49 አመት የሆናቸው 23.6% ሴቶች እና 16.8% ወንዶች ግርዛት የሃይማኖታቸው መስፈርት እንደሆነ ያምናሉ። ይህም እምነት በአብዛኛው በሙስሊም ወንድና ሴቶች ዘንድ የተለመደ ነው።[18] የሴት ልጅ ግርዛት እንዲካሄድ በጣም ጠንካራው ድጋፍ ያለው የአፋር፣ የሶማሌ እና የሲዳማ ሴቶች እና የአፋር፣ የሶማሌ እና የአማራ ወንዶች ዘንድ ነው።[19] በአፋር ክልል አብዛኛው ህዝብ በሚገኝበት ስፍራ ስለ ሴት ልጅ ግርዛት የጤና ጉዳት መረጃ መስጠት እና ሙስሊም የሃይማኖት መሪዎች መልእክት እንዲያስተላልፉ ማድረግ ያመጣው ለውጥ መኖሩ የሃይማኖት መሪዎችን በፕሮግራም ውስጥ ማሳተፍ ያለውን ጠቀሜታ የሚጠቁሙ ምልክቶች ናቸው።[20]

የሴት ልጅ ግርዛትን የሚያራምዱ ማህበራዊ እና ባህላዊ ልምምዶችን ለመቅረፍ የሚደረጉ እርምጃዎች የእያንዳንዱን ብሔረሰብ እምነት እና ተግባር መሰረት ያደረጉ መሆን አለባቸው። ይህን የሚያስፈጽሙ አካላት እና አክቲቪስቶች ድርጊቱን በማስቀረት ሂደት ውስጥ የሚያስከትለውን ከባድ ማህበራዊ መዘዝ መረዳት አለባቸው።

ተግባራዊ እርምጃው በሀገሪቱ ውስጥ በሚገኙ የሴት ልጅ ግርዛት ቦታዎች ላይ ትኩረት ማድረግ አለበት፣ በአብዛኛዎቹ ጉዳዮች ላይ ሃይማኖታዊ እምነቶች የድርጊቱ ጠንከር ያሉ አንቀሳቃሾች ናቸው። ለማስተማር እና አመለካከትን ለመቀየር በእነዚህ አካባቢዎች የሃይማኖት መሪዎችን ማሳተፍ ወሳኝ ነው።

አብዛኛዎቹ ኢትዮጵያውያን ልጃገረዶች እድሜያቸው ከ 5 አመት በታች ሆነው ነው የሚገረዙት።[21] ከ15-49 ዓመት ከሆናቸውና የሴት ልጅ ግርዛት እንደ ተፈጸመባቸው ሪፖርት ከተደረጉት ኢትዮጵያውያን ሴቶች መካከል 73% የሚሆኑት ሴቶች አካላቸው ተቆርጦ ተወግዷል። 2.6% ያህሉ እንደ የተቆረጡ ሲሆን፣ ነገር ግን ሥጋቸው አልተወገደም፤ እና 6.5% 'የተሰፉ' (የተሰፋ ወይም የዓለም ጤና ድርጅት በወጣው ደረጃ መሰረት 3ኛው ዓይነት) ሪፖርት ተደርጓል። 17.9% የሚሆኑት ደግሞ ምን አይነት የሴት ልጅ ግርዛት እንደተደረገባቸው አያውቁም።[22] የተሰፉ ሴቶች እና ልጃገረዶች በብዛት ከሶማሌ(75.6%) እና ከአፋር (71%) ብሄረሰቦች የተውጣጡ ከ15-49 አመት እድሜ ያላቸው ሴቶች ናቸው። ሙስሊም ሴቶች ከሌላ እምነት ተከታዮች በበለጠ የመገረዝ እድላቸው ሰፊ ነው።[23]

ከህጉ አንፃር በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ከአንቀጽ 565 እስከ 570 በተደነገገው መሰረት የሴት ልጅ ግርዛት ህገ-ወጥ ነው።[24] በዚህ መሰረት መንግስት እና ዩኒሴፍ በ2011 ዓ.ም ያለዕድሜ ጋብቻን እና ግርዛትን ለማስቆም ከ 2012-2016 ዓ.ም የሚቆይ በብሔራዊ ወጪ ፍኖተ ካርታ አዘጋጅተዋል። ይህም ልጃገረዶች እና ቤተሰቦቻቸውን በማብቃት ከ2017 ዓ.ም በፊት ግርዛትን እና ያለ እድሜ ጋብቻን ለማስወገድ ያለመ ነው። በተጨማሪም ከማህበረሰቡ ጋር (የእምነት መሪዎችን ጨምሮ); በየደረጃዉ ያሉ የመንግስት ሴክተሮች ውስጥ ያሉ ስርዓቶችን ተጠያቂነትን እና አገልግሎቶችን ማሳደግ፣ ምቹ አካባቢዎችን መፍጠር እና ማጠናከር; እና መረጃዎችን ማመንጨት እና አጠቃቀም መጨመርን ያካትታል።[25] ምንም እንኳን ወንጀለኛ ባይደረጉም በህክምና የተደረጉ የሴት ልጅ ግርዛት በጥር 2017 በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ታግዷል።[26] መንግስት የሴት ልጅ ግርዛትን ለማጥፋት ምቹ ሁኔታን የበለጠ ለመፍጠር ከተፈለገ፤ ህግን የማስከበር እና የህግ አገልግሎት ተደራሽነትን ማሻሻል አለበት።[27]

ኢትዮጵያ በጤና እና ደህንነት ረገድ በዘላቂ ልማት ግቦች ላይ የተወሰነ እድገት አሳይታለች። በስርዓተ-ፆታ እኩልነት መረጃ ጠቋሚ ከ144 ሀገራት 125ኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች፤ እና በአሁኑ ወቅት በጣም ዝቅተኛ ደረጃ አለው።[28] ይህ ማለት በኢትዮጵያ ውስጥ ላሉት ሴቶች በሁሉም አህጉር ካሉ ሴቶች ይልቅ ሁኔታዎች ፈታኝ ናቸው። በኢትዮጵያ ያለው የሴት ልጅ ግርዛት ስርጭት ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ ሀገራት ከአማካይ በላይ ሲሆን የአፍሪካ ቀንድ ሲታሰብ ግን በኢትዮጵያ ያለው ስርጭት ከአብዛኞቹ ጎረቤቶቿ ያነሰ ነው። እንደ አለመታደል ሆኖ፣ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ በጾታ እኩልነት ላይ፣ ትምህርት ቤቶችን በመዝጋትያመጣው መጥፎ ተፅዕኖ እስከ አስር ሚሊዮን የሚደርሱ ልጃገረዶች ለያለዕድሜ ጋብቻ እና ለሴት ልጅ ግርዛት የመጋለጥ እድላቸውን ከፍ አድርጓል።[29] የእናቶች ሞት መጠን ጨምሯል። በአዎንታዊ መልኩ የጨቅላ ህጻናት ሞት መጠን ቀንሷል፤ እናም በ2007 ከሚሊኒየሙ የልማት ግቦች ከተቀመጠው የመጨረሻ ጊዜ ከሶስት አመታት በፊት፣ ኢትዮጵያ ከአምስት አመት በታች ላሉ ህጻናት ሞት መቀነስ ላይ ግቧን መታለች።

የሴት ልጅ ግርዛትን ለማጥፋት የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም እየሰሩ ያሉ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አሉ። እነርሱም የሴት ልጅ ግርዛትን ለማስወገድ ሀገራዊና ክልላዊ ቅስቀሳዎችን በማድረግ፣ የድርጊቱን ብሔር ተኮር አንቀሳቃሾች ጋር በመወያየት፣ የአባቶችን የሥርዓተ-ፆታ ደንቦችን በማስተናገድ፣ በትምህርትን በማስተዋወቅ፣ ላይ የሚገኙ በርካታ ዓለም አቀፍ እና የሀገር ውስጥ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አሉ። የእነዚህ አካሄዶች አጠቃላይ እይታ፣ ጥሩ ከሚሰሩ ድርጅቶች ምሳሌዎች ጋር በዚህ ዘገባ ውስጥ ተካትቷል።

ይህ ሪፖርት የሚከተሉት ተግባራዊ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ይጠይቃል:

- በኢትዮጵያ የሴት ልጅ ግርዛትን ለመከላከል የፋይናንስ ምንጮችን **ማሳደግ**፣ እድገትን ለማፋጠን ዘርፈ ብዙ ምላሽ መስጠት
- እንደ አካባቢያዊ የስርጭት መጠን **ዒላማ** ማድረግ፤
- የንዑስ ክልላዊ መረጃዎችን **መሰብሰብ** እና **ጥቅም ላይ ማዋል፤**
- በእያንዳንዱ ማህበረሰብ ውስጥ ካለው አሠራር ጋር ከተያያዙ **ልዩ** ሁኔታዎች እና አውድ ጋር መሳተፍ፤
- ስለ ሴት ልጅ ግርዛት አመለካከቶችን እና እምነቶችን ለመመርመር በተዘዋዋሪ መንገድ በመጠቀም የምርምር ዘዴዎችን **ማሻሻል**፤
- ወንዶችንና ወጣት ወንዶችን፣ የሃይማኖት መሪዎችን እና ተደማጭ የማህበረሰብ አባላትን በማሳተፍ ያልተገረዙ ሴቶችን እና ልጃገረዶችን ከማህበራዊ መገለል አደጋን **መቀነስ፤**
- የማህበረሰብ ውይይቶችን እና የክህሎት ስልጠናዎችን ከግንኙነት ጋር **በማቀናጀት** የሴት ልጅ ግርዛትን ግንዛቤ ማሳደግ፣
- የሴቶች እና ልጃገረዶች ኢኮኖሚያዊ እድሎችን **ማጠናከር** እና **ማሳደግ**።

# References


1 African Development Bank Group (2022) *Ethiopia Economic Outlook* (sourced from the African Economic Outlook 2022. Available at https://www.afdb.org/en/countries/east-africa/ethiopia/ethiopia-economic-outlook.

2 UNDP (2021) 'Ethiopia', *Human Development Reports*. Available at https://hdr.undp.org/data-center/specific-country-data#/countries/ETH.

3 BBC News (2021) *Ethiopia election: Abiy Ahmed wins with huge majority*, 11 July. Available at https://www.bbc.com/news/world-africa-57791868.

4 UN Office of the High Commissioner for Human Rights (2021) *Report of the Ethiopian Human Rights Commission (EHRC)/Office of the United Nations High Commissioner for Human Rights (OHCHR) Joint Investigation into Alleged Violations of International Human Rights, Humanitarian and Refugee Law Committed by all Parties*. ReliefWeb. Available at https://reliefweb.int/report/ethiopia/report-ethiopian-human-rights-commission-ehrcoffice-united-nations-high-commissioner.

5 Al Jazeera (2022) *UN: Warring sides committing atrocities in Ethiopia's Tigray*, 19 September.

Available at https://www.aljazeera.com/news/2022/9/19/un-warring-sides-committing-atrocities-in-ethiopias-tigray.

6 The Independent (2023) *Ethiopia church split resolved amid social media suspension*, 16 February. AP News Wire. Available at https://www.independent.co.uk/news/ap-oromia-ethiopia-nairobi-kenya-b2283730.html.

7 Zelalem Shiferaw Woldemichael (2022) 'Unlawful detention of journalists in Ethiopia continues despite amended laws', *Ethiopia Insight*, 11 December. Available at https://www.ethiopia-insight.com/2022/12/11/restrictions-on-journalists-in-ethiopia-continue-despiteamendedlaws/#:~:text=Under%20the%20new%20law%2C%20criminal,torture%20during%20pre%2Dtrial%20detention.

8 Reporters Without Borders (2021) *Ethiopia*. Available at https://rsf.org/en/country/ethiopia.

9
- Maggie Flick (2021) 'In Abiy's Ethiopia, press freedom flourished then fear returned', *Reuters*, 28 May. Available at https://www.reuters.com/world/africa/abiys-ethiopia-press-freedom-flourished-then-fear-returned-2021-05-28/.
- Zelalem Shiferaw Woldemichael (2022), *op. cit.*
- Muthoki Mumo (2022) 'Journalists face growing hostility as Ethiopia's civil war persists', *Committee to Protect Journalists*, 1 August. Available at https://cpj.org/2022/08/journalists-face-growing-hostility-as-ethiopias-civil-war-persists/.

10
- Maggie Flick (2021), *op. cit.*
- Zelalem Shiferaw Woldemichael (2022), *op. cit.*

11 #KeepItOn coalition (2023) *Open letter to the Ethiopian Government: urgently end ongoing internet shutdowns in all regions across the country*, 27 April. Access Now. Available at https://www.accessnow.org/press-release/open-letter-to-the-ethiopian-government/.

12 DHS 2016, pp.47–48.

13
- DHS 2000, p.33.
- DHS 2005, p.253.
- DHS 2016, p.321.

14
- DHS 2000, p.33.
- DHS 2016, p.321.

15 DHS 2016, p.327.

16
- Mhairi A. Gibson, Eshetu Gurmu, Beatriz Cobo, María M. Rueda and Isabel M. Scott (2018) 'Indirect questioning method reveals hidden support for female genital cutting in South Central Ethiopia', *PLoS ONE*, 13(5). https://doi.org/10.1371/journal.pone.0193985.
- Elisabetta De Cao and Clemens Lutz (2018) 'Sensitive Survey Questions: Measuring Attitudes Regarding Female Genital Cutting Through a List Experiment', *Oxford Bulletin of Economics and Statistics*, 80, pp.871–892. https://doi.org/10.1111/obes.12228.

17 Elizabeth Presler-Marshall, Nicola Jones, Erin Oakley, Rebecca Dutton, Sarah Baird, Workneh Yadete and Yitagesu Gebeyehu (2022) *Exploring the diversity of FGM/C practices in Ethiopia: Drivers, experiences and opportunities for social norm change*. London: Gender and Adolescence: Global Evidence. Available at https://www.gage.odi.org/publication/exploring-the-diversity-of-fgm-c-practices-in-ethiopia-drivers-experiences-and-opportunities-for-social-norm-change.

18 DHS 2016, p.326.

19 DHS 2016, p.327.

20 Elizabeth Presler-Marshall, Nicola Jones, Erin Oakley, Rebecca Dutton, Sarah Baird, Workneh Yadete and Yitagesu Gebeyehu (2022) *Exploring the diversity of FGM/ C practices in Ethiopia. Drivers, experiences and opportunities for social norm change*, p.6. London: Gender and Adolescence: Global Evidence. Available at https://www.gage.odi.org/publication/exploring-the-diversity-of-fgm-c-practices-in-ethiopia-drivers-experiences-and-opportunities-for-social-norm-change.

21 DHS 2016, p.322.

22 DHS 2016, p.321.

23 DHS 2016, p.321.
24 *The Criminal Code of the Federal Democratic Republic of Ethiopia* (2004). Available at https://www.ilo.org/dyn/natlex/docs/ELECTRONIC/70993/75092/F1429731028/ETH70993.pdf.
25 Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Women, Children and Youth (2019) *SUMMARY: National Costed Roadmap to End Child Marriage and FGM/C 2020–2024*. Available at https://ethiopia.un.org/sites/default/files/2019-09/Roadmap%20to%20end%20child%20marriage%20and%20FGM%20summary%20Unicef%20.pdf.
26 UNICEF (2021) *The Medicalization of FGM In Kenya, Somalia, Ethiopia and Eritrea*. Available at https://www.unicef.org/esa/media/8866/file/The-Medicalization-of-FGM-2021.pdf.
27 UNJP (2021) *Delivering and Sustaining in the New Normal: 2021 Annual Report and Phase III Performance Analysis*. Available at https://www.unfpa.org/sites/default/files/pub-pdf/FGM- AR2021.pdf.
28 Equal Measures 2030 (2022) *2022 Gender Index: Back to Normal is Not Good Enough*, p.19. Available at https://www.equalmeasures2030.org/wp-content/uploads/2022/03/SDG-index_report_FINAL_EN.pdf.
29 Jeffrey D. Sachs, Christian Kroll, Guillaume Lafortune, Grayson Fuller and Finn Woelm (2021) *Sustainable Development Report 2021: The Decade of Action for the Sustainable Development Goals*. Cambridge University Press. DOI 10.1017/97. Available at https://unstats.un.org/sdgs/report/2020/The-Sustainable-Development-Goals-Report-2020.pdf.

This update is intended to be used in conjunction with and as a supplement to the report **Country Profile: FGM in Ethiopia** published by 28 Too Many (part of Orchid Project) in 2013, which may be downloaded at https://www.fgmcri.org/country/ethiopia/.

This publication is licensed under a CC BY-NC 4.0 licence. Extracts from it may be freely reproduced, provided that due acknowledgement is given to the source and Orchid Project. We seek updates on the data and invite comments on the content and suggestions on how our reports can be improved.

For more information, please contact us at research@orchidproject.org.

---

**Authors**: Shannon Thomson, Sean Callaghan, Danica Issell, Melanie Rattue.

**Recommended citation:** Orchid Project (2023) *FGM/C in Ethiopia: Country Profile Update, June 2023*. Available at www.fgmcri.org/country/ethiopia/.

*Please note the use of a photograph of any girl or woman in this Country Profile Update does not imply that she has, nor has not, undergone FGM/C.*

#NOFGM

**© Orchid Project 2023; Version 1, October 2023**
***This work is licensed under a CC BY-NC 4.0 licence.***
research@orchidproject.org